"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቆጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

# 811- PRAC/የኪራይ ድጋፍ ፕሮጀክት/ ውል
# የአካለስንኩላን የድጋፍ መኖሪያ ቤት

ከአሁን በኋላ አከራዩ /ላንድ ሎርድ/ ተብሎ በሚጠራው በ__________(B)__________እና ተከራዩ /ቴናንት/ ተብሎ በሚጠራው በ_______(C)_________________ መካከል በ _______(A)_________ቀንና 20_________ዓ.ም ይህ የስምምነት ውል ተፈጽሟል::

ምስክሮች:

ከቤቶችና ከተማ ልማት (HUD) ሴክሬተሪያት/ከአሁን በኋላ ሴክሬተሪያት ተብሎ በሚጠራው/ በኩል በብሄራዊ ተዳራሽ ቤቶች ህግ (National Affordable Housing Act) / በ1992 ቱ የቤቶችና ህብረተሰብ ልማት ህግ (Housing and Community Development Act) እንደተሻሻለው/ ክፍል 811 መሠረት ለአከራዩ የካፒታል ቅድመ ክፍያ በሚያስጠውና ከዚህ በኃላ የሚብራራውን ይህን የመኖሪያ ቦታ unit የሚገኝበትን ፕሮጀክት በሚሸፍነው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣን በሚመለከት አከራዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሰጭ በመሆኑ፣

አከራዩ የኪራይ ድጋፍ ፕሮጀክት (PRAC) ውል ከሴክራትሪያት ጋር የተዋዋለ በመሆኑ፤

የዚህን ውል አፈጻጸም መቆጣጠርን በተመለከተ አከራዩና ሴክሬተሪያቱ መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት አከራዩ በብሄራዊ ተዳራሽ ቤቶች ህግ /በ1992ቱ የቤቶችና ህብረተሰብ ልማት ህግ እንደተሻሻለው/ ክፍል 811 እንዲሁም የ HUD ት መመሪያዎች ውስጥ ስለ ተከራዩ ድጋፍ ወደሚደረግበት የመኖሪያ ቦታና ይህንኑ በ PRAC ውል ቃላትና ድንጋጌዎች መሠረት በቀጣይነት ይዞ ስለመቆየት ሁኔታዎች በሚያዘው መሰረት መኖሪያ ቦታው በፕሮጀክቱ ውስጥ በሚታቀፉ አካለስንኩላን ይዞታ ስር እንዲሆን ለመወሰን ተከራዩ የተስማማ በመሆኑ፤

ስለሆነም፣

1. _____________(D)_____________ተብሎ የሚጠራውን የፕሮጀክቱን የመኖሪያ ቤቶችን ከ_(E)_________, ቀን 20________ዓ.ም ጀምሮ በ____(F)____________ቀን 20______ዓ.ም እንዲያልቅ ሆኖ ለአንድ ዓመት አከራዩ ለተከራዩ ሲያከራይ፤ ተከራዩም ከአከራዩ ይህንኑ ተከራይቷል::

2. አጠቃላይ የወሩ የኪራይ ክፍያ $_(G)____________ዶላር ይሆናል::

3. ይህ በአንቀፅ 2 የተጠቀሰው የኪራዩ መጠን ቀጥሎ ያሉትን የግልጋሎት ወጪዎችን ይጨምራል::

___________(H)____________________ ________________________________

(አጠቃላዩ የወሩ የኪራይ ክፍያ ሁሉንም የግልጋሎት ወጪዎችን የሚያጠቃልል ከሆነ "ሁሉንም" የሚለውን ቃል ይሙሉበት፤ ነገር ግን ተከራዩ በከፊልም ይሁን በሙሉ የግልጋሎት ወጪዎችን ለብቻው ለይቶ የሚከፍል ከሆነ ግን ቀጥሎ ያለውን አንቀፅ እንደ "3A"ያስገቡት::)

እዚህ የተገለፀው አጠቃላዩ ኪራይ የአገልግሎት ወጪዎች አሎዋንሱ $__(I)_______ ዶላር የሆነውን ግልጋሎቶችን አይጨምርም:: እነሱም፤

________(J)____________________________ _______________________________________
______________________________________ _______________________________________

እነዚህን ግልጋሎቶች የሚመለከቱ ዕዳዎች ተከራዩ አገልግሎቱን ለሰጠው ኩባንያ/ዎች/ በቀጥታ መክፈል አለበት:: የግልጋሎት አሎዋንሱ የ HUD ባጸደቀዉ ቅደም ተከተልና ዝርዝር መስፈርት መሠረት ሲታይ የተከራዩን አጠቃላይ ተያያዥ የቤት ወጪዎችን የክፊያ ድርሻ በልጦ የተገኘ እንደሆነ አከራዩ ልዩነቱን/በብልጫነት የታየውን ወጪ/ መንግሥትን በመወከል ወይም በመንግሥት ፈንታ በመሆን ከ HUD ለዚሁ ዓላማ የተመደበውን ገንዘብ ተቀብሎ ለተከራዩ መክፈል አለበት::

4. ከአጠቃላይ የኪራዩ ክፍያ ውስጥ $_____(K)_________ ዶላር በተከራዩ ፈንታ የ HUD ወይም እሱ በሚያዘው መሠረት ለፕሮጀክቱ የኪራይ ክፍያ ድጋፍ በሚል ይፈፀምለታል:: የተቀረው $____________(L)____ ዶላር በተከራዩ በራሱ ይሸፈናል:: ይህ የተጠቀሰው የክፍያ መጠን የ HUD መስፈርት ከተቀያየረ፤ የ HUD ባወጣው የሚታወቁ ቅደም ተከተልና መሥፈርት መሠረት የተከራዩ ቤተሰብ ገቢ ወይም የቤተሰብ ብዛት ቢቀያየር ወይም ለየት ያለ የሕክምና ወይም ሌላ ያልተጠበቀ ወጪ ቢያጋጥም፤ ወይም ማንኛውም በውሉ የተመለከተው የአገልግሎት አሎዋንስ ላይ የከተማ ቤቶችና ልማት ማስተካከያ ያደረገ እንደሆነ የኪራዩ የክፍያ መጠን ሊለወጥ ይችላል:: እነዚህ ለውጦች ለተከራዩ በማስታወቂያ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

5. ተከራዩ የራሱን የኪራይ ዕዳ ድርሻ ለአከራዩ በወሩ መጀመሪያ ቀን ወይም ከዚያ በፊት በ______(M)____________________ ወይም አከራዩ በጽሁፍ በየጊዜው ለሚያሳውቀው ሌላ/ሎች/ ሰው/ዎች/ ወይም ቦታ መክፈል አለበት::

6. ይህ ውል ስፈረም ተከራዩ 50 ዶላር ወይም የአንድ ወሩን ኪራይ/ከ50 ዶላር የሚበልጥ ከሆነ/ በመያዣነት መስጠት አለበት:: በዚሁ መሠረት ከተከራዩ፣ ከቤተሰቡ፣ ከእንግዶቹ ወይም ከወኪሎቹ የንብረት አጠቃቀም የተነሳ ከሚመጣ መጠነኛ እርጅና በቀር ንብረት ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ግምት በሙሉ ከመክፈል ግዴታ ጋር $_____(N)____________________ዶላር በመያዣነት አስቀምጧል:: ይህ ውል ሲቋረጥ የመያዣ ገንዘቡ ለተከራዩ ይመለሳል ወይም በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ክፍያ ይውላል ወይም ሳልተከፈለ ክፍያ ማጣጫ ይውላል:: በመያዣ ገንዘብ ላይ ስለሚከፈል ወለድ የወጡ የስቴትና የአካባቢ ሕጎች አከራዩ ላይ ተፈፃሚነት አለው / አከራዩ ይፈጽማል/::

7. አከራዩ በሚሰጠው አገልግሎት ወይም በማንኛውም ሌላ አኳኋን ዘርን፣ ቀለምን፣አቋምን፣ እምነትን፣ የቤተሰብ ሁኔታን፣ አመጣጡን ወይም አካለስንኩልነቱን መሠረት በማድረግ በተከራዩ ላይ አድልዎ ማድረግ የለበትም::

8. በዚህ ውል እንደተገለጸው ውሉ እንዲቋረጥ ወይም እንዲሻሻል ካልተደረገ በቀር ይህ ስምምነት ወዲያው በያንዳንዱ ተከታታይ ወር ይታደሣል፤ ሆኖም ግን ከዚህ በታች በተገለፀው መሠረት ውሉ ማስተካከያ ልደረግበት ይችላል::

(a) ይህን ውል ተከራይ በመጀመሪያ ዙር ወይም በየትኛውም ዙር ስምምነት መጨረሻ ላይ የ30 ቀን የጽሁፍ ማስታወቂያውን ለአከራዩ በመስጠት ማቋረጥ ይችላል:: አከራዩ በግልፅ ይህንን ስምምነት የጣሰ እንደሆነ ተከራዩ በስቴት ህግ መሠረት ለአከራዩ በጽሁፍ ገልጾ ውሉን ማቋረጥ ይችላል::

(b) አከራዩ ይህን ውል የማቋረጥ መብቱ የሚገዛው በሴክሬቴሪያቱ ደንብ 24 CFR 891.430 እና Part 247 /ከዚህ በኋላ የ HUD ደንብ ተብሎ በሚጠቀስው /ነው:: በ HUD ደንብ አከራዩ ቀጥሎ ባሉት ምክንያቶች ብቻ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል ተደንግጓል:: እነሱም፤

(1) አከራዩ ከዚህ በታች በአንቀፅ (g) በተገለፀው መሠረት "ይህ ውል አይታደሥም:: ስለሆነም በዚሁ ውሉ መቋረጡን አሳውቅሃለሁ" ብሎ ለተከራዩ በመግለፅ የመጀመሪያ ዙር የውል ዘመን ወይም ሌላ ተከታይ የውል ዘመን ሲያልቅ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል:: ይህ አይነት የውል ማቋረጥ የሚቻለው ግልፅ የሆነ የውል መጣስ፣ የስቴቱ የአከራይ ወይም ተከራይ ሕግ የሚጥለውን ግዴታ በግልፅ አለመወጣት፣ ለተከራየው ሥፍራ በቅርበት የሚኖሩ ሰዎች ከሚፈፅሙት የወንጀል ተግባር የተነሣ የነዋሪዎቹ ጤና፣ ደህንነት እና በሠላም በደሥታ የመኖር መብታቸው ሥጋት ላይ የወደቀ እንደሆነ፣ በሥፍራው ንብረቱን የሚያስተዳድሩ ሰራተኞችን ጤንነትና ደህንነት ሥጋት ላይ የጣለ የወንጀል ተግባር፣ በነዋሪው ወይም በነዋሪው የቤተሰብ አባላት ወይም በነዋሪው ቁጥጥር ሥር ባለ ማንኛውም ሰው በዚያው በመኖሪያ ሥፍራ ወይም በአቅራቢያው ከአደንዛዥ ዕፅ ጋር የተያያዘ ወንጀል መፈፀም፣ ወይም "በሌላ አሣማኝ ምክንያት " መሰረት ውሉን ማቋረጥ ይቻላል:: የውሉ መቋረጥ "በሌላ አሣማኝ ምክንያት " በሚል የሆነ እንደሆነ የውሉን መቋረጥ ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሉን ስለማቋረጥ በተገለፀው የዚህ ስምምነት አንቀፆች መሠረት በውሉ ዘመን መጨረሻ መሆን አለበት:: ሆኖም ግን ይህ የውል ማቋረጥ ሀሳብ በአከራዩ ለተከራዩ ከተገለፀለት ጊዜ ጀምሮ በምንም አይነት ከ30 ቀናት በፊት መሆን የለበትም:: የውሉ ማቋረጥ ማስታወቂያዉ ምክንያቱ በግልፅ ይህን ውል የመጣስ ወይም የስቴቱ የአከራይ እና ተከራይ ሕግ የሚጥለውን ግዴታ ያለመወጣት የሆነ እንደ ሆነ ማስታወቂያ መስጫ ጊዜ የሚወሰነው ከዚህ በላይ ባለው ዐረፍተ ነገር ወይም የስቴቱ ሕግ ከሁለቱም በኋለኛው /በኋላ በወጣው/ መሠረት ይሆናል::

(2) በንዑስ አንቀፅ(1) ከፍ ብሎ የተገለፀው ቢኖርም ተከራዩ በግልፅ ይህንን ውል በጣሰ ጊዜ ሁሉ አከራዩ በስቴቱ ሕግ ወይም በ HUD ደንቦች መሠረት እታች በፊደል (g) እንደተገለፀው ማስታወቂያ ሰጥቶ ይህን ውል ማቋረጥ ይችላል::

(c) ተከራዩ ኪራዩ ሲቋረጥ ከተከራየበት ስፍራ መልቀቅ ባለበት ቀን ያልለቀቀ እንደሆነ አከራዩ የስቴቱ ወይም የአካባቢው ሕግ ከሥፍራ ስለማስለቀቅ በሚያዘው መሠረት እና በ HUD ደንብ የተቀመጠውን መመዘኛ ተከትሎ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ሊወስደው ይችላል::

(d) "በግልፅ ይህንን ስምምነት መጣስ" የሚለው ሐረግ ተከራዩን በሚመለከት ቀጥሎ ያሉትን ያጠቃልላል፤ (1) አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የዚህ ውል መሠረታዊ ጥሰት፣ (2) የዚህን ፕሮጀክት ቀጣይነት የሚያደናቅፍ ፣ የማንኛውንም ሰው ጤና ወይም ደህንነት ወይም የማንኛውንም ተከራይ በኪራዩ ሥፍራ እና ተያያዥ የፕሮጀክቱ ፋሲሊቲዎች የመጠቀም መብቱን በእጅጉ የሚጎዳ፣ ፕሮጀክቱን በማስተዳደር ሥራ ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ወይም ፕሮጀክቱ ላይ ከፍ ያለ ወጪን የሚያስከትል ተደጋጋሚ አነስተኛ የስምምነት ግዴታዎች ጥሰት፣ (3) ገቢንና የቤተሰብ ብዛትን ወይም የተከራዩ ቤተሰብ አባላትን አስፈላጊ መስፈርት የሚያሟሉ መሆን አለመሆናቸውን የሚመለከቱ ተፈላጊ መረጃዎችን በሙሉ ተከራዩ በተፈለገ ጊዜ ሣያቀርብ መቅረት /ይህም በ 24 CFR Part 5, Subpart B መሰረት የሶሻል ሴኩሪቲን ቁጥር ስለመግለፅና ስለማረጋገጥ የተደነገገውን አለማክበር ወይም ሆን ብሎ ያልተማላ ወይም ትክክል ያልሆነ መረጃ መስጠትን ያጠቃልላል::/ በስቴቱ ሕግ መሠረት ለዕዳ መክፈያ ከሚፈቀደው ማንኛውም ተጨማሪ ጊዜ በላይ አልፎ የኪራዩን ዕዳ ወይም ከዚህ ውል የመነጨ ማንኛውም የገንዘብ ክፍያን/ከፊሉንም ቢሆን/ አለመወጣት መሠረታዊ የውል መጣስ ተደርጎ ይቆጣጠራል:: የኪራዩ ዕዳ ወይንም ከዚህ ውል የመነጨ ማንኛውም የገንዘብ ክፊያ መከፈል ካለበት ቀን በኋላ ነገር ግን በስቴቱ ለዕዳ መክፈያ በሚፈቀደው ተጨማሪ የጊዜ ገደብ ውስጥ የተከፈለ እንደሆነ እንደአነስተኛ የውል መጣስ ይቆጠራል::

"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቆጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

(e) የተከራዩ ባህሪይ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ አከራዩ ካልገለፀለት በቀር የተከራዩን ባሕሪይ ውልን ለማቋረጥ እንደ "ሌላ አሳማኝ ምክንያት" ለመቁጠር አይቻልም:: ይህ ለተከራዩ የማስታወቁ ተግባር የሚከናወነው ከዚህ በታች በአንቀጽ (g)በተገለጸው አኳኋን መሆን አለበት::

(f) አከራዩ ይህን ውል ለማቋረጥ ያለውን ውሳኔ በፅሑፍ አድርጎ፣ (1) ስምምነቱ በዚህ ውል በተጠቀሰው ቀን መቋረጡን መግለጽ፣(2) ተከራዩ የራሱን የመቃወሚያ ሃሳብ ማቅረብ ይችል ዘንድ አከራዩ ውሉን የሚያቋርጥበትን ምክንያት በበቂ ዝርዝር፣(3) ተከራዩ እስከ ውሉ ማቋረጫ የመጨረሻ ቀን ድረስ የተከራየውን ሥፍራ ለቆ ሣይወጣ የቀረ እንደሆነ ይህንኑ በሚመለከት መቃወሚያ ካለውም እዚያው ማቅረብ እንዲችል አከራዩ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ብቻ በመውሰድ ተገዶ እንዲለቅ ማድረግ እንደሚችል አከራዩ ለተከራዩ ማሳወቅ፣(4) አከራዩ ይህን የማሳወቅ ተግባሩን ለተከራዩ በግልፅ ከዚህ በታች በአንቀፅ (g) በተገለፀዉ አኳኋን መፈጸም አለበት::

(g) የአከራዩ የውል ማቋረጥ ማስታወቂያው መፈፀም ያለበት፤ (1) የላኪው አድራሻ በአግባቡ የተፃፈበት፣ በአግባቡ ማህተም የተደረገበት እና የተቀባዩ አድራሻ የተፃፈበት የተመዘገበ ደብዳቤ በፕሮጀክቱ በኩል ለተከራዩ በመላክና (2)የዚሁኑ ማስታወቂያው ኮፒ ከተከራዩ ቤት /ክፍል/ ውስጥ መጥቶ በር ለሚከፍት ማንኛውም አዋቂ ሰው በመስጠት ወይም ማንም አዋቂ ሰው ያልተገኘ እንደሆነ ማስታወቂያውን በበር ውስጥ ወይም ሥር በመክተት ወይም በር ላይ በመለጠፍ ይሆናል:: እነዚሁ ሁለቱ የማስታወቂያዎች አገላለፅ ሥርዓት እስከሚፈፀም ድረስ ማስታወቂያው ውጤት አይኖውም:: ተከራዩ ማስታወቂያውን እንደተቀበለ የሚቆጠረው በተራ ቁጥር (1) መሠረት ደብዳቤ የተላከበት ቀን ወይም በተራ ቁጥር (2)መሠረት ማስታወቂያው የተሰጠበት ቀን ማለትም ከሁለቱ የኋለኛው የተፈፀመበት ቀን ነው::

(h) አከራዩ በ HUD ካስፀደቀ በኋላ ከመጀመሪያው የውል ዘመን ወይም ቀጥሎ ካሉት የውል ዘመኖች መጨረሻ ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን የውሉን ማሠሪያ ሐሳቦችንና ሁኔታዎችን ማሻሻል የሚችለው ተገቢ ማስታወቂያ ከዚሁ ከተጠቀሰው የማሻሻያ ሐሳብ ማስታወሻ ጋር አያይዞ ወይም ማስተካከያዎችን ጭምር ለተከራዩ ሲያስታውቀው ነው:: ማንኛውም የኪራይ ጭማሪ ሁሌም በ24 CFR Part 245 እና ሌሎች ተፈፃሚነት ባላቸዉ የ HUD ደንቦች መገዛት አለበት:: ይህ ማስታወቂያና የማሻሻያው ማስታወሻ ለተከራዩ በተፃፈ ህግና ሁኔታዎች ሣይከለከል (እላይ በ /g/ በተገለፀው መሠረት) ውሉን ለማቋረጥ መብት ከሚያገኝዉ የመጨረሻው ቀን በፊት ቢያንስ 30 ቀን ቀደም ብሎ መሆን አለበት:: ተከራዩ በአከራዩ የተገለፁለትን የስምምነት ማሻሻያ ማስታወሻ ወይም ማስተካከያዎችን ተቀብሎ በመፈፀም መቀበሉን /መስማማቱን/ ሊገልፅ ወይም አልቀበልም ማለቱን የሚገልፅ ፅሑፍ ውሉን ለማቋረጥ ካሰበበት ከ30 ቀን በፊት ለአከራዩ መስጠት ይችላል:: የተከራዩ የውል ማቋረጥ ማስታወቂያው መፈፀም ያለበት በአግባቡ የአከራዩ አድራሻ ተፅፎበትና ማህተም ተመትቶበት በአድራሻው መሆን አለበት::

(i) አከራዩ ይህን ውል ቀጥሎ ባሉት ምክንያቶች ሊያቋርጥ ይችላል::

1. በማንኛውም ተከራይ ወይም የቤተሰብ አባል ወይም እንግዳ ከአደንዛዥ ዕፅ ጋር የተያያዘ የወንጀል ድርጊት በኪራዩ ስፍራ ወይም በአጠገቡ መፈፀም እና ማንኛዉም እንደዚህ ዓይነት ድርጊት በተከራዩ ቁጥጥር ስር ባለ ሌላ ሰው በኪራዩ ስፍራ መፈፀም፣

2. በተከራየው ቤት ውስጥ የሚኖሩት የቤተሰብ አባላት በሕገወጥ መንገድ አደንዛዥ መድሃኒት /ዕጽ/ ይጠቀማሉ ብሎ አከራዩ ከወሰነ፣

"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቀጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

3. የህገ ወጥ አደንዛዥ መድሃኒት አጠቃቀም በተከራየው ሥፍራ ላይ የሚኖሩ የሌሎች ነዋሪዎችን ጤና፣ ደህንነትና በደስታ የመኖር መብታቸው ላይ ደንቃራ ስለመሆኑ አከራዩ የወሰነ እንደሆነ፣

4. በተከራዩ፣ በማንኛውም የተከራዩ ቤተሰብ አባል፣ በእንግዳው አከራዩ ወይም ሌላ በተከራዩ ቁጥጥር ሥር ባለ ሰው ወንጀል በመፈፀሙ፣

(a) እዚያው በስፍራው የሚኖሩ የንብረት አስተዳደር ሰራተኞችን ጨምሮ በሌሎች የሥፍራው ነዋሪዎች ጤና፣ ደህንነት፣ ወይም በደስታ የመኖር መብታቸውን ሥጋት ላይ የጣለ እንደሆነ፤ ወይም

(b) በቅርብ አቅራቢያው በራሳቸው መኖሪያ የሚኖሩ ሰዎችን ጤና፣ ደህንነት እና በደስታ የመኖር መብታቸውን ሥጋት ላይ የጣለ እንደሆነ፤

5. ተከራዩ ለወንጀል ወይም ለወንጀል ድርጊት ሙከራ ከመከሰስ፣ ከእሥራት ወይም በቁጥጥር ሥር ከመዋል እየሸሸ እንደሆነ ይህ ግለሰብ እየሸሸ ለነበረበት ቦታ ህግ ይህ ድርጊቱ ከባድ ወንጀል ወይም በኒዉርጀርሲ ሕግ መሠረት ደግሞ አንስተኛ ወንጀል ነው::

6. ተከራዩ በገደብ ከእሥራት የተለቀቀበትን ሁኔታ ወይም በአመክሮ እንዲቆይ የሚደነግገውን የፌዴራል ወይም የስቴት ህግ የጣሰ እንሆነ፣

7. የተከራዩ የቤተሰብ አባላት የአልኮል አጠቃቀም በተከራየው ሥፍራ ላይ በሚኖሩ ሌሎች ነዋሪዎች ጤና፣ ደህንነት እና በደስታ የመኖር መብታቸዉ ላይ ሥጋት ጥሏል ብሎ አከራዩ የወሰነ እንደሆነ፣

8. ተከራዩ፣ የተከራዩ የትኛውም የቤተሰብ አባል፣ እንግዳ፣ ወይም ሌላ በተከራዩ ቁጥጥር ሥር ያለ ሰው ለሠራው ወንጀል የተያዘ ወይም የተፈረደበት እንኳ ቢሆን ማንኛውም የተከራዩ የቤተሰብ አባል፣ እንግዳ፣ በተከራዩ ቁጥጥር ሥር ያለ ሌላ ሰው ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ፣

9. ተከራዩ የቤተሰቡ ገቢ፣ የቤተሰቡ ብዛትና ሌሎች መስፈርቶች ተከራዩ ለመክፈል ከሚገደደው የኪራይ መጠንና የቦታው ይዞታ መብት አንፃር መሰረታዊና ግልፅ ግዴታ እንደምጥልበትና በ HUD ደንብና መስፈርት መሰረት ከተከራየበት ጊዜ ጀምሮ አመታዊ የገቢ ማረጋገጫዎች ለአከራዩ እንደምሰጥ (ተከራዩ) ስምምነቱን ገልጿል::

10. ተከራዩ እራሱ ባሳወቀበት የገቢ ለውጥ ማሥረጃ መሠረት አከራዩ የተከራዩን የወር የኪራይ ድርሻ ክፊያዉን ሊያሻሽልበት እንደሚችልና በማሻሻያውም ተከራዩ ሊገዛ/ሊያከብር/ ተስማምቷል:: አከራዩ ይህንኑ ማሻሻያን የሚመለከት ፅሁፍ ከ30 ቀን ቀድሞ ለከተራዩ የውሉ አካል ማስተካከያ በማድረግ ተከራዩ ምን ያህል በየወሩ መክፈል እንዳለበት ሊያሳውቀው ተስማምቷል::

"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቆጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

11. ተከራዩ ይህን የውል መብቱን ለሌላ ማስተላለፍ፣ የውሉን ሥፍራ መከፋፈል፣ ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ወይም ማረፊያ ማድረግ ወይም ከተከራዩና ከቤተሰቡ ማረፊያነት ውጭ ለሌላ አላማ መጠቀም አይችልም:: ተከራዩ በውሉ በተረከባቸዉ እነዚሁ ክፍሎች ለመኖርና ለራሱና ለቤተሰቡ ብቸኛ መኖሪያ እንዲሆን ተስማምቷል::

12. (a) ተከራዩ የመጀመሪያ ገቢውን የሚመለከት ሰነድ ወይም ማረጋገጫ ወይም ማንኛውንም ሌላ የተጭበረበረ መረጃ ለአከራዩ ከሰጠ፣(b) ተከራዩ ተፈላጊ የገቢ ማረጋገጫ ወይም መረጃ ተጠይቆ ሳይሰጥ ሲቀር ካልሆነ በቀር ተከራዩ ለአከራዩ መክፈል ያለበትን የአኪራዩን ዕዳ ለመክፈል ተስማምቷል::

13. ተከራዩ ለራሱ /ሷ/ እና ለወራሹ/ሿ/ ለሚያስፈጽሙለትና ለአስተዳዳሪዎቹ ቀጥሎ እንደተመለከተው ተስማምቷል፣

(a) ተከራዩ የአከራዩን የኪራይ ክፊያ ምንም ሳይቀናንስ እና አከራዩ ክፈለኝ እንጂ ብሎ እንዲጠይቅ ሣይጠበቅበት መክፈል ባለበት ጊዜ ወዲያው ለመክፈል፣

(b) የኪራዩን ሥፍራ በጥራትና በንጽህና ለመጠበቅ እና ይህንኑ በውሉ የተመለከተውን ሥፍራና የትንንሽ ተያያዝ ቦታዎችን ጤንነትንና ደህንነትን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት ባላቸዉ የህንጻና የቤቶች ደንቦች እንዲሁም የህግ ድንጋጌዎችንና መስፈርቶችን ወይም መመሪያዎችን ከመጣስና ካለማክበሩ የሚመነጩ የገንዘብ መቀጮ፣ቅጣትና ወጪዎች እንዲሁም ከእንደዚህ ዓይነት ጥሰትና ህግን ካለማክበር የሚመነጭ ተጠያቂነት አከራዩ ላይ እንዳይመጠ ለማድረግ ተስማምቷል::

(c) ለመኖሪያ ሥፍራው ኢንሹራንስ መዲን በሰጠው ኩባንያ አደገኛ ነዉ ሊባል ለሚችል አላማ ቦታዉን አለመዋል::

(d) ከተከራዩ ተግባር ወይም ቸልተኛነት የተነሣ በንብረት ላይ ማንኛውም ዓይነት ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ተከራዩ እራሱ ይህንን ጉዳት መጠገን / ማሰራት/አለበት፤ ይህ ሣይሆን ቀርቶ ተከራዩ ጉዳቱ በደረሰ በምክንያታዊ የጊዜ ገደብ ወስጥ ያላስጠገነ ወይም ማስጠ ገን እምቢ ያለ እንደሆነ አከራዩ በገዛ ፈቃዱ ጥገናውን አከናውኖ ለዚሁ ያወጣውን ወጪ ከተከራዩ ይጠይቀዋል:: ተከራዩም ይህንኑ ጥገና የሚመለከት ወጪ ለአከራዩ መተካት አለበት::

(e) አከራዩን፣ ወይም ወኪሉን ወይም የአከራዩን የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ /ሞርጌጅ/ የያዘን ሰው ተወካይ / በአከራዩ የተፈቀደለት እንደሆነ/፣ የኮንትራክተር ሠራተኞችን፣ የግልጋሎት ኩባንያዎችችን፣ የማዘጋጃ ወኪሎችን ወይም ሌሎችን ወደ ተከራየው ሥፍራ ምክንያታዊ የንብረት ፍተሻ ለማድረግ እና ለጥገናና ለመተካት ሥራዎች ዓላማ እንዲገቡ መፍቀድ አለበት::

(f) ያለ አከራዩ ቅድመ ፈቃድ የማጠቢያ ማሽን፣ የልብስ ማድረቂያ፣ የአየር ሙቀትና ቅዝቃዜ መቆጣጠሪያ ዘዴ በአፓርትመንቱ ላለመትከል፤ እና

(g) ተከራዩ የዚህን ውል ቃል ወይም ድንጋጌዎችን የጣሰ ወይም ለመጣስ የዛተ እንደሆነ አከራዩ ወይም ወኪሉ/ሏ/ ተገቢ የሆነ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ ለመፍቀድ ተስማምቷል::

“ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቆጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።”

14. በ 24 CFR Part 5, Subpart C ድንጋጌዎችና በ 24 CFR 5.315 ስለ አብሮ-በል የቤት እንስሳት (pets) የወጣው መመርያ እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራዩ መደበኛ የሆኑ አብሮ-በል የቤት እንስሳትን በኪራዩ ስፍራ ማኖር ተፈቅዶለታል:: የፕሮጀክቱ ባለቤት በያንዳንዱ የጋራ ቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉት አብ-ሮበል እንስሳት ቁጥር አንድ ብቻ እንዲሆን መወሰን ይችላል::(24 CFR 5.318(b)(ii)). ማንኛውም በአከራዩ የወጡ የቤት አንስሳት መመርያ የዚህ ውል አባሪና አካል ሆነዋል.፣ ተከራዩም በነዚህ መመርያዎች ሊገዛ ተስማምቷል:: ይህን መመርያ መጣስ በ 24 CFR Part 5, Subpart C እና ተፈፃሚነት ባላቸው መመሪያዎች እና በስቴቱ ወይም በአከባቢው ህግ መሠረት የአብ-ሮበል የቤት እንስሳትን ከኪራዩ ሥፍራ ማስወገድ ወይም የኪራዩን ውል ማቋረጥ ወይም ሁለቱንም ለማድረግ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: እነዚህ መመሪያዎች 24 CFR Part 247 / የተወሰነ ዲጎማ ከሚደረግባቸው እና በ HUD ባለቤትነት ሥር ካሉ ፕሮጀክት ስለማስለቀቅ/ እና የውል ማቋረጥን ሚመለከቱ ድንጋጌዎችና የፕሮጀክቱ ኪራይ ድጋፍ ውልን ያጠቃልላል.::

ማስታወሻ.፣ የአብሮ-በል የቤት እንስሳት ደንብ ክፍል 5 በአካለ ስንኩልነት ምክንያት ከተከራዩ ወይም ከእንግዳ ጋር መሆን ያለበትን እንስሳ አይጨምርም::

/ የፈለገው ሊጨምረው የሚችለው ሀሳብ Optional /አከራዩ በቂ ማስታወቂያ ለተከራዩ ከሰጠ በኋላ አግባብ ባለው ሰዓት ወደተከራዩ ሥፍራ መግባትና ዕቃዎችን ማየት ይችላል:: ወደ ሥፍራው መግባትና ዕቃዎችን ማየት ለአከራዩ የሚፈቀደው በመኖሪያ ሥፍራው የአብሮ-በል እንስሳቱ ባህሪይና ሁኔታ በአካባቢው ህግ መሠረት በፕሮጀክቱ ሥፍራ ነዋሪዎች ወይም ፕሮጀክቱ ባለበት አካባቢ ላሉ የቤተሰብ አባላት ስለማወኩ ወይም ለጤናቸው አደጋ ስለመደቀኑ የፅሑፍ አቤቱታ ሲደርሰው ወይም አከራዩ በአሳማኝ ምክንያት ይህንኑ ያመነ እንደ ሆነ ነው::

ሰውን ሊያጠቃ የሚችል ወይም የጤና መታወክ ምልክት የሚታይበት ወይም ከአጠቃላዩ የኪራዩ አፈፃፀም አንፃር በጤናና ደህንነት ላይ አይቀሬ አደጋ የደቀነ ባህሪይ የሚታይበት አብሮ-በል እንስሳን የማስወገድ ሥልጣን በስቴቱ ወይም በአከባቢው ህግ የተሰጣቸው የስቴቱ ወይም የአከባቢው ባለሥልጣናት ወይም ህጋዊ ተወካይ የሌለ እንደሆነ አከራዩ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ወደ ኪራዩ ስፍራው በመግባት ይህንኑ አብሮ በል እንሰሳ ማስወገድ፤ ወይም የስቴቱና የአከባቢው ህግ በሚፈቅደው መሠረት በአብሮ በል እንስሳ ላይ ለእንስሳው ደህንነት ማቆያና መጠለልያ የሚሆን ቦታ ላይ ከ30 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ ማቆየትን ጨምሮ እርምጃ መውሰድ ይችላል:: አከራዩ ወደስፍራው በመግባት ይህን አብሮ በል እንስሳ ማስወገድ ወይም ሌላ የተፈቀደ እርምጃ መውሰድ የሚችለው እንስሳውን ወዲያውኑ ከፕሮጀክቱ እንዲያስወግደው ተከራዩ በአከራዩ ተጠይቆ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፣ወይም ይህን እንሰሳ አስወግድልኝ ለማለት ተከራዩን ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው:: ለእንስሳው ደህንነት ማቆያ የወጣ ወጪ በ 24 CFR 5.363 በተደነገገው መሠረት ሊከፍል ይገባል:: ማሳሳቢያ: አንቀጽ 14 ለያንዳንዱ የ811 የጋራ ቤቶች ኗሪዎች ላይ ተፈፃምነት የለዉም::

15. አከራዩ ተፈፃሚነት ባላቸዉ የፌዴራል፣ የስቴት እና የአካባቢ እንድሁም የጤና፣የቤቶችንና የግንባታ ደንቦችን ጨምሮ የሚያስቀምጡትን መስፈርቶች በሙሉ ለማክበር ተስማምቷል::

16. ተከራዩ ይህን ውል በመፈፀም የመኖሪያን ክፍል/ቦታውን/ አይቶ/ፈትሾ/ እንዳፀደቀ አምኖ ይቀበላል:: ተከራዩ ይህ የክራይ ስፍራ በአጥጋቢ ሁኔታ እንደተጠናቀቀና.፣ አከራዩን ቀለም እንዲቀባለት፣ እንዲያስለጣጥፍለት ወይም ማንኛውንም ሌላ የጉልበት ሥራ፣ ወይም ቀድሞውንም የተፈጸመለትን አገልግሎት እንዲሰጠው አይጠይቅም:: አከራዩ ገና ከጅምሩ ክፍሉን ፈተሾ አይቶ በጥሩ ሁኔታ ሊከራይ በሚችልበት ሁኔታ ማግኘቱን አምኖ ይቀበላል:: እንዲሁም ይህንኑ ይዞታ ምክንያታዊ እርጅና እና ጉዳትን ሳይጨምር በተረከበበት ጥሩ ሁኔታ መልሶ ለአከራዩ ለማስረከብ ተስማምቷል::

"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቀጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

17. ከአከራዩ በፅሑፍ የሆነ ቅድመ ፈቃድ ካልተሰጠ በቀር በመኖሪያው ሥፍራ ውስጥም ሆነ ውጪ ለውጥ፣ ጭማሪ ወይም ማሻሻያ ማድረግ አይችልም:: አከራዩ አካለ ስንኩል ለሆነው ተከራይ ምክንያታዊ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል መመሪያዎችን፣ የፖሊሲዎችንና የሥነ ሥርዓቶችን ለውጥ ጨምሮ የመኖሪያ ክፍሉን አሰራር መቀየር ወይም የጋራ መጠቀሚያ ቦታዎችን ለመሥራትና ለዚሁ ሥራ ክፊያ ለመፈፀም ተስማምቷል::አከራዩ የራሱ ፕሮግራም ላይ ሥር-ነቀል ለውጥ ወይም ከፍ ያለ የገንዘብና አስተዳደራዊ ጫና የሚያስከትል የአካለ ስንኩላን ማስተናገኛ እንዲያቀርብ አይጠበቅበትም::የደንቡን 24 CFR Part 8 ይመልከቱ:: በተጨማሪ የተጠየቀው የክፍሎቹ አሰራር ለውጥ ከፍ ያለ የገንዘብና የአስተዳደራዊ ጫና የሚያስከትል የሆነ እንደሆነ ተከራዩ ይህንኑ እንዲሰራና ለለውጡ የሚወጣው ወጪ በፍትሀዊ የቤቶች ህግ/ ፍቷፀረ ህጼጭሰፀነገ ጽቸተሐ መሠረት እንዲከፍል አከራዩ የግድ መፍቀድ አለበት::

18. ተከራዩ በአከራዩ የተሟሉለትን የቤት መገልገያዎች እንዳይባክኑ አግባብነት ለሌላቸው ወይም ላልተፈቀደ ዓላማ ላለመጠቀም፣ እና ያለአከራዩ ፈቃድ ቤቱ ላይ የሚሰካኩ ነገሮችን እንድሁም ምልክቶችን ፣በውስጥ ወይም በመኖሪያው ዙሪያ አጥር ላለማድረግ ተስማምቷል::

19. የኪራዩን ስፍራ በማይንቀሳቀስ ንብረት የእዳ መያዣነት ተይዞ ወይም ሊያዝ ከሆነ ይህ የክራይ ስምምነት በሁለተኛ ደረጃ መታየት የለበትና የእንዲህ ዓይነት መያዣዎች መመዝገብ ከዚህ ስምምነት ይልቅ ለመያዣዉ ቅዲሚያና የበላይነት የሚሰጥና፣ ለዕዳ ክፍያ ሲያዝም ቅዲሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ተከራይ ይህን ውል ከመያዘዉ አንፃር የበለጠ በሁለተኛ ደረጃ እንድታይ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንዲህ ዓይነቱን የመያዣ ሰነድ ተከራዩ የለምንም ወጪ ተግባራዊ ማድረግ ያለበት ሆኖ ይህን አላደርግም ያለ እንደሆነ አከራዩ ወይንም ከሱ መብት የተለለፈለት ሰውና ህጋዊ ወኪሉ ከፈለጉ ይህን ውል የመሰረዝ ስልጣን የሚሰጣቸዉ ሆኖ ይህን መብት የሚያጎናፅፋቸው ይህ አባባል በግልፅ በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ተወስኖ ይፈፀማል::

20. የአከራዩ በዚህ ውል ውስጥ የተጠቀሱ ሐሳቦችን፣ ቃልኪዳኖችንንና ሁኔታዎችን ወይም ከነዚህ አንዱን በጥብቅ ሳይፈጽም መቅረት አከራዩ እነዚህን ሃሳቦች፣ ቃልኪዳኖችና እና ስምምነቶችን ወይም ሁኔታዎችን እንደማይፈልጋቸው ተደርገውበት ሊታዩ ወይም በሙሉ ይዘቱ ውሉን መቀጠልና መፈፀም እንጂ አከራዩ በመብቱ ሌሎችን ሊያስገድድበት አይችልበትም አይባልም::

21. ተከራዩ ያለማቋረጥ የዚህን ውል ሃሳቦችና ሁኔታዎችን ለሚፈፅመው ምላሽ እንዲሆን አከራዩ ይህን ውል ፀንቶ በሚቆይባቸው ጊዜያት ሁሉ ከላይ የተገለፀውን ንበረት ተከራዩ ለራሱ ጥቅምና አገልግሎት እንዲያውለው ቃል ይገባል::

22. የተከራዩን ገቢ ስለማረጋገጥ፤ ስለ የቤተሰብ አባል የገቢ መጠን መረጃ በተመለከተ ከ HUD የተላከን ማንኛውንም ደብዳቤ ወይም ሌላ ማስታወቂያ ወይም በ HUD መስፈርት መሰረት የቤተሰብ ገቢ ማረጋገጫን ተከራዩ ወዲያውኑ ለአከራዪ መስጠት አለበት::

"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቆጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

23. የተከራዮች የመደራጀት መብት፣ የተከራዩች አደራጆች የተከራዮችን መደራጀት የሚመለከቱ ተግባራትን በንብረቱ ላይ በቤቶችና ከተማ ልማት መስፈርት መሰረት ማከናወን እንዲቻል አከራዩ ፈቅዷል::

24. በሂደት የሚፈጠሩ ነገሮችን ስለማረጋገጥ፤

a. ቀጥሎ ካሉት አንዱ ክስተት እንኳ ቢቀየር አከራዩ ተከራዩን ሊያማክር/ሊያሳውቀው/ ተስማምቷል፤

1. ማንኛዉም የቤተሰብ አባል ከቤቱ ለቅቆ የወጣ እንደሆነ፤

2. በቅርብ ጊዜ በተሰጠ መረጃ ወይንም ማረጋገጫ ሥራዓጥ ነው ተብሎ የነበረ አዋቂ የቤተሰብ አባል ሥራ ያገኘ እንደሆነ፤

3. የቤተሰብ አባላት አጠቃላይ ገቢ በ $200 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ የጨመረ እንደሆነ፣

b. ተከራዩ ማንኛዉንም የገቢ መቀነስ ወይም በተከራዩ የኪራይ ክፊያ ስሌት ወቅት ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ሌሎች ሁኔታዎችን መቀያየር / መለዋወጥ/ ሪፖርት ሊያረግ ይችላል:: ይህን የገቢ መቀነስ ወይም የሁኔታዎች መቀያየር የቆየው ከአንድ ወር ላነሰ ጊዜ መሆኑን ማረጋገጫ ያለው ካልሆነ በቀር አከራዩ እነዚህን መረጃዎች በማረጋረጥ ተገቢ የኪራይ ቅነሳ ማድረግ አለበት::ሆኖም ግን የተከራዩ ገቢ በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ በሁለት ወራት ውስጥ ወደነበረበት የቀድሞ ደረጃ የተመለሰ እንደሆነ አከራዩ የማረጋገጡን ሂደት አዲሱ የገቢ መጠን እስከሚታወቅ ሊያዘገየው ይችላል:: ነገር ግን የኪራዩ ክፊያ መቀነሱ ወደ ኋላ ተመልሶ የገቢው መጠን ለቀነሰባቸው ጊዜያት እና ይህንኑ በማረጋገጡ ሂደት ወቅት ሳይከፈል ለቀረው ኪራይ ዕዳ ሲል አከራዩ ተከራዩን የኪራዩን ቦታ ለቀህ ውጣልኝ ሊለው አይችልም:: ተከራዩ ከላይ ለተገለፀው ጊዜ መክፈል ያለበትን ኪራይ እንዲከፍል የፅሁፍ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ይህንኑ ለመክፈል 30 ቀናት ይኖሩታል ወይም ይህንኑ የኪራይ ክፊያ ባለመክፈሉ ምክንያት አከራዩ ከሥፍራው ሊያስለቅቀው ይችላል::

c. ተከራዩ የቤተሰቡ አባላትን ወይም የገቢ መጨመርን በተመለከተ በሂደት የተከሰቱ ለውጦችን ለአከራዩ ያላሳወቀ እንደሆነ ከኪራዩ ስፍራው እንዲለቅ ሊደረግ ይችላል::አከራዩ ተከራዩን ከሥፍራው ሊያስለቅቀው የሚችለው ከ HUD ደንቦች፣ የሥራ ጥራዞች ውስጥ በተቀመጠው የጊዜ ማዕቀፍና አስተዳደራዊ ሥነ ሥርዓት ብቻ ነው::

d. ማንኛዉም የገቢ ወይንም የሌሎች ሁኔታዎች መቀያየረ እንዴት የተከራዩን ኪራይ ወይም የድጋፍ ክፊያዉን ሊጎዳበት እንደሚችል ለመነጋገር እንገናኝ ብሎ ተከራዩ አከራዩን ሊጠይቀው ይችላል::ተከራዩ የዚህ ዓይነት የእንገናኝ ጥያቄ አቅርቦ እንደሆነ አከራዩ ከተከራዩ ጋር ተገናኝቶ ኪራዩ ወይንም የድጋፍ ክፊያው /ያለዉ እንደሆነ/ እንዴት እንደተሰላ ለማብራራት ተስማምቷል::

25. የስምምነቱ አባሪዎች፤ ተከራዩ የዚህን ስምምነት ኮፒና ቀጥሎ ያሉትን አባሪዎች ከመቀበሉም በተጨማሪ እነዚህ አባሪዎች የስምምነቱ አካል እንደሆኑ ተረድቷል::

a. አባሪ ተራ ቁጥር 1 – የ HUD የተከራይ ተቀባይነትንና የኪራይ ሥነ ሥርዓትን የሚመለከት ቅፅ፤

b. አባሪ ተራ ቁጥር 2 – የመኖሪያ ክፍሎቹ የተፈተሸበት/የታየበት/ሪፖርት፤

"ይህ ሰነድ በHUD ለወጣው ህጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም የሚያቀርበው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን እንዲረዱ ዘንድ ለመርዳት ሲል ብቻ ነው። የእንግሊዘኛ ቋንቋ እትም ህጋዊ፣ ዋናና ተቆጣጣሪ ነው። የተተረጎመው ሰነድ ህጋዊ ሰነድ አይደለም።"

c. **አባሪ ተራ ቁጥር 3 - የቤት መመሪያዎች/ያለ እንደሆነ/**

d. **አባሪ ተራ ቁጥር 4 - የአብሮ-በል የቤት እንስሳት ደንቦች፤**

"የኪራዩ የፊርማ መስመር ተሰርዟል"

**ሕዝባዊ ሪፖርት የማቅረብ ጫና** - የኪራይ ውሎቹ አጠቃቀም በቤት ኪራይ ኢንደስትሪው የተለመደ አሠራር ስለሆነ HUD ለኪራይ ናሙናዎቹ ለማንኛውም የጫና ሰዓቶች ፈቃድ እየጠየቀ አይደለም። ይህ መረጃ ጥቅሞችን ለማግኘት አስፈላጊ ነው። የተጠየቀው እና አስፈላጊ የድጋፍ ሰነዶች ፈቃድ ለማግኘት ወደ HUD ወይም ውል አስተዳዳሪው (Contract Administrator) ይላካሉ። የኪራዩ ውል በፕሮጀክቱ ባለቤት እና በተከራዩ(ዮቹ) መካከል በዩኒት ውስጥ ለመኖር ሊከበሩ የሚገባቸውን ስምምነቶች የሚያብራራ ውል ነው። የኪራይ ውሎች በቤት ኪራይ ኢንደስትሪ ውስጥ የተለመዱ የአሠራር ሂደቶች ናቸው። ባለቤቶች የHUD የኪራይ ውል ናሙና መጠቀም ያለባቸው ሲሆን ናሙናው በቤት ኪራይ ኢንደስትሪው ውስጥ የሚሠራባቸውን የውል ስምምነቶች እንዲሁም ፕሮጀክቱ የተገነባበት ፕሮግራም እና/ወይም ለተከራዮች የኪራይ እገዛ የሚሰጥበት ፕሮግራም ውስጥ እንዲካተቱ HUD የሚፈልጋቸውን ስምምነቶች ያቀፈ ነው።

ይህ መረጃ የተፈቀደው በ24 CFR 5.360፣ 236.750፣ 880.606፣ 883.701፣ 884.215፣ 886.127፣ 891.425 891.625 and 891.765 የኪራይ ሽፋን መስፈርቶችና አቅራቦቶች ነው። ይህ መረጃ ጥብቅና ልዩ መከላከያ የሚያስፈልገው አይደለም።